# Storybooks Canada

storybookscanada.ca

## ዓመት በዓልን ከአያት ጋር

Written by: Violet Otieno
Illustrated by: Catherine Groenewald
Translated by: Dawit Girma

This story originates from the African Storybook (africanstorybook.org) and is brought to you by Storybooks Canada in an effort to provide children's stories in Canada's many languages.

This work is licensed under a Creative Commons Attribution 4.0 International License.
https://creativecommons.org/licenses/by/4.0

# ዓመት በዓልን ከአያት ጋር

Violet Otieno
Catherine Groenewald
Dawit Girma
Amharic
Level 4

(imageless edition)

ኦዶንጎና አፒዮ ከአባታቸው ጋር ከተማ ነው የሚኖሩት። ዓመት በዓልን በጉጉት ይጠብቃሉ። ትምህርት ስለሚዘጋ ሳይሆን በዚያ አጋጣሚ አያታቸውን የማየት እድል ስለሚያገኙ ነው። የሴት አያታቸው አሳ በሚመረትበት መንደር ከትልቁ ሐይቅ አጠገብ ይኖራሉ።

ኦዶንጎና አፒዮ በጣም ተደስተዋል ምክንያቱም እንደገና አያታቸውን ሊጎበኙ ነው። በዋዜማው ማታ ሻንጣቸውን ሸካክፈው ወደ አያታቸው ቀዬ ለሚያደርጉት ረጂም ጉዞ ተዘጋጁ። አልተኙም፤ ሌሊቱን ሙሉ ስለበዓሉ ሲያወሩ አደሩ።

በነጋታው ጠዋት በአባታቸው መኪና ሆነው ጉዞ ጀመሩ። ተራራውን እያቆራረጡ፣ የዱር እንስሳትና የሻይቅጠል ማሳዎችን አልፈው እየሄዱ ነው። የሚያልፉ መኪናዎችን እየቆጠሩ፣ መዝሙር እየዘመሩ ነው የሚሄዱት።



ኦዶንጎ እና አፒዮ ወደ ትምህርት ቤት ሲመለሱ ለጓደኞቻቸው አገር ቤት ስለነበራቸው ቆይታ ነገሯቸው። አንዳንድ ልጆች የከተማ ህይወት ጥሩ እንደሆነ ያስባሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ገጠር የተሻለ እንደሆነ ይሰማቸዋል። ሁሉም ሰው ኦዶንጎ እና አፒዮ በጣም ግሩም የሆኑ አያት እንዳላቸው ይስማማሉ።

ኦዶንጎ እና አፒዮ ጥብቅ አድርገው አቀፏቸውና ተሰናበቷቸው።



ከጊዜ በኋላ ልጆቹ ደከማቸውና ተኙ።

ከመንደሯ ሲደርሱ አባታቸው ቀሰቀሳቸው። አያታቸው እመት ንያር ካንያዳ ዛፍ ጥላ ስር ምንጣፍ ላይ ቁጭ ብላ ረፍት ስታደርግ አገኟት። ጠንካራና ቆንጆ ሴትዮ ናት።



አባታቸው ሊወስዳቸው ሲመጣ እነሱ በበኩላቸው መሄድ አልፈለጉም። ልጆቹ ንያር ካንያዳን አብራቸው ወደ ከተማ እንድትሄድ ጠየቀቻቸው። ፈገግ አለችና እንዲህ አለች፣ ‹‹አይ ልጆቼ ከተማ ለመኖር እንኳ አርጅቻለሁ። ዳግም ወደኔ ዘንድ እስክትመጡ እጠብቃችኋለሁ።››

ብዙም ሳይቆዩ በዓላቱም አለፉ፤ ልጆቹም ወደ ከተማ መመለሻቸው ሆነ። ንያር ካንያዳ ለኦዶንጎ ኮፍያ፣ ለአፒዮ ደግሞ ሹራብ ሰጠቻቸው። ለመንገዳቸውም ስንቅ ቋጠረችላቸው።



ንያር ካንያዳ በክብር ወደቤቷ አስገባቻቸውና በደስታ መዝፈን ያዘች። የልጅ ልጆቿ ከከተማ የገዙላትን ስጦታዎች በደስታ ሰጧት። <<መጀመሪያ የእኔን ስጦታ ክፈችው>> አለ ኦዶንጎ። <<አይደለም፣ መጀመሪያ የኔን>> አለች አፒዮ።

ስጦታዎችን ከከፈተች በኋላ አያትዬው የልጅ ልጆቿን መረቀቻቸው።



ሲጨርሱ ሁሉም በአንድ ላይ ሆነው ሻይ ጠጡ። አያታቸው ከሽያጯ ያገኘችውን ገንዘብ በመቁጠር አገዟት።

በሌላ ቀን ልጆቹ ከአያታቸው ጋር ወደገበያ ወጡ። የሚሸጥ ቅጠላቅጠል፣ ስኳርና ሳሙና ይዛለች። አብይ ለደንበኞቹ የሚሸጡ ነገሮችን ዋጋ ይናገራል። አፒዮ ደግሞ የተሸጡ እቃዎችን ለገዢዎች ትጠቀልልላቸዋለች።



ከዚያም አዱኛና አፒዮ ወደ ውጪ ወጡ። ቢራቢሮዎችንና ወፎችን ማባረር ያዙ።

ዛፍ ላይ ይወጣሉ፤ ሐይቁ ውስጥም ይንቦጫረቁ ነበር።



አንድ ቀን ጠዋት ኦዶንጎ የአያቱን ላሞች ሳር ለማጋጥ ወደመስክ ወሰዳቸው። ላሞቹም ወደጎረቤት ማሳ ሮጠው ገቡ። የማሳው ባለቤት ገበሬ በኦዶንጎ ተናደደበት። አስፈራራው፣ ሰብሉን ስለበሉበት ላሞቹን እንደሚወስድበት አስፈራራው። ከዚያ ቀን በኋላ ላሞቹ ዳግም ችግር እንዳይገጥማቸው ይጠነቀቅ ጀመር።

ንያር ካንያዳ የተለያዩ ምግብ አሰራሮችን ለልጆቹ አስተማረቻቸው። ሩዝና የተጠበሰ አሳ አሰራር እንዴት እንደሚሰራ አሳየቻቸው።



ሲመሽ ለራት ወደ ቤት መጡ። ምግባቸውን በወጉ ከመጨረሳቸው በፊት እንቅልፍ ጣላቸው።

በሚቀጥለው ቀን አባታቸው ልጆቹን ከአያታቸው ጋር ትቷቸው ወደ ከተማ ተመለሰ።



ኦዶንጎና አፒዮ አያታቸውን ቤት ውስጥ ስራ ያግዟቸው ነበር። ውሃ ይቀዳሉ፣ የማገዶ እንጨትም ይለቅማሉ። ዶሮዎች የጣሉትን እንቁላሎች ይሰበስባሉ፣ ቅጠላቅጠል ከአትክልት ስፍራው ይሰበስባሉ።